# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ

# የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት

## የክበባት ጥምረት ማቋቋሚያ

## መመሪያ

ታህሳስ 2013

አዲስ አበባ

# መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ ወጣቶች ከተለያዩ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ተላቀው በከተማዋና በሀገራዊ ልማት ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማእከላት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የሚታመን በመሆኑ፣

ማእከላቱ ወጣቶች ጊዜያቸውን በንባብና ወቅታዊ መረጃዎችን በመቃኘት የስነተዋልዶ ጤና እንዲሁም በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ... ኤድስ ምክርና ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆንና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት ጤነኛና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ በሚደረገው ጥረት በሚያግዙበት መልክ እንዲቃኙና እንዲመሩ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት የተቋቋሙ ክበባት በጋራ መድረክ እርስ በእርስ ልምድና ተሞክሮዎቻቸውን የሚጋሩበት፣ ተደጋግፈው በመስራት በተደራጀ አኳኋን በስራዎቻቸው ወጣቶችንና ህብረተሰቡን መድረስ የሚችሉበት፣ በአሰራር፣ አደረጃጀትና የድጋፍ ስርዓት የሚጠናከሩበት ጥምረት መፍጠር በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ይህንን የክበባት ጥምረት መመስረቻ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

## የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ክበባት ጥምረት መመስረቻ መመሪያ

እኛ ስማችንና ፊርማችን በዚህ ሰነድ መጨረሻ ገጽ ላይ የተመለከተው ክበባት በአንቀጽ 2 የተገለጸውን ጥምረት መስርተናል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   የወጣቶች ስብእና መገንቢያ ማእከላት የክበባት ጥምረት መመስረቻ መመሪያ ቁጥር-- 2013 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1. **"ከተማ"**፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
2. **"ቢሮ"** ፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ማለት ነው፡፡
3. **"ጽ/ቤት"**፡-ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ስር የተቋቋመ የክፍለ ከተማ የወጣቶችና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና የወረዳ ወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡
4. **"ወጣት"** ፡- ማለት እደሜያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት ባለው የእድሜ ክልል ውስዋ ያሉ ማለት ነው፡፡
5. **ክበብ"**፡-ወጣቶች በተፈጥሮ የታደሏቸውን የጥበብና ተሰጥኦ ክህሎቶች የሚያዳብሩባቸውን እድል የሚፈጥር አደረጃጀት ነዉ፡፡
6. **"ጥምረት"**፡- ማለት በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ውስጥ የተቋቋሙ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ክበባት በአሰራር፣ አደረጃጀትና የድጋፍ ስርዓት ራሳቸውን ለማጠናከር የሚፈጥሩት ህብረት ነው፡፡
7. **"ጠቅላላ ጉባኤ"**፡- ማለት በየደረጃው ተመራጭ የሆኑ የክበባት ጥምረት ዋና ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና ባለድርሻ አካላት የጋራ ምክክር የሚያደርጉበትና የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት የጥምረቱ የበላይ ጠባቂ አካል ማለት ነው፡፡
8. **"የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከል"**፡- ማለት በከተማ አስተዳደሩ የተገነባ እንዲሁም መንግስታዊ ባልሆኑ ሌሎች አካላት ተገንብተው ለከተማ አስተዳደሩ

የተላለፈ የት/ት ስልጠና የምክር የመረጃ የስፖርትና መዝናኛ እና መሰል ወጣት ተኮር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ አንድ

## ስለመቋቋም፡፡

ጥምረቱ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 404 መሰረት በ------ቀን-----ዓ.ም ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ ሁለት

## ስያሜ፡፡

ይህ የጥምረት መመስረቻ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ የወረዳ----------ወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል የክበባት ጥምረት በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ጥምረት ተብሎ ይጠራል፡፡

## አንቀጽ ሦስት

## አድራሻ፡፡

የጥምረቱ ዋና መስሪያቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ----------ክፍለ ከተማ በወረዳ------------ ወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ይገኛል፡፡

የፖስታ ሳጥን ቁጥር----------------------------

የስልክ ቁጥር-------------------------------------

ፌስቡክ -----------------------------------------

ቴሌግራም------------------------------

## አንቀጽ አራት

## የጥምረቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፡፡

ጥምረቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

4.1. ወጣቶች በተፈጥሮ የታደሏቸውን የጥበብና ተሰጥኦ ክህሎቶች የሚያዳብሩባቸውን እድሎች እንዲያገኙ ከማዕከሉ፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር መስራት፡፡

4.2. ክበባት የፈጠራ ስራዎቻቸውንና ማህበራዊ አገልግሎቶቻቸውን ለህዝብ ማስተዋወቅ የሚችሉባቸው ፌስቲቫሎችና መሰል መድረኮች እንዲመቻቹላቸው ማድረግ፡፡

4.3. ክበባት የሀገራቸውን ወግ፣ ባህል፣ ታሪክና ልዩ ልዩ ክዋኔዎች የሚለማመዱበትና ሀገራዊና አለማቀፋዊ የተሞክሮ ልውውጥ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

4.4. ክበባት በጋራ፣ በትብብርና መረዳዳት መንፈስ በመስራት ውጤታማ እንዲሆኑና ለከተማዋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፡፡

4.5. ሁለንተናዊ ስብዕናቸው የተገነባ ሰብአዊነትን የተላበሱ፣ የኪነ-ጥበብና ፈጠራ ባለሙያዎችን ማፍራት፡፡

## አንቀጽ አምስት

## የክበባት ጥምረት መዋቅር

ጥምረቱ በሚከተለው አደረጃጀት የተዋቀረ ነው፡፡

ጥምረቱ በወረዳ ደረጃ በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል፣ በክፍለ ከተማና በከተማ ደረጃ የሚደራጅ ሲሆን የጥምረቱ አባል ክበባት በወረዳ፣በክፍለ ከተማና በከተማ ደረጃ ከመካከላቸው የስራአስፈጻሚ ከሚቴ አባላት በመምረጥ ያቋቁማሉ፡፡የወረዳ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ክበባት ጥምረት ስራአስፈጻሚ ኮሚቴዎች በክፍለ ከተማ ደረጃ ፣የክፍለ ከተማ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች በከተማ ደረጃ የአዲስ አበባ ወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ክበባት ጥምረትን ይመሰርታሉ፡፡ ጥምረቱ በየደረጃው በሚኖረው አደረጃጀት የሚከተለው መዋቅር ይኖረዋል፡፡

ሀ/. ጠቅላላ ጉባኤ

ለ/. የስራአስፈጻሚ ኮሚቴ

ሐ/. ኦዲተር

## አንቀጽ ስድስት

### 6. ጠቅላላ ጉባኤ

ጥምረቱ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለማስፈጸም ጠንካራና ዲሞክራሲያዊ አሰራር ተገዥ የሆነ አመራር ሰጪ አካል ሊኖረው ይገባል፡፡በዚሁ መሰረት የጥምረቱን የስራ እንቅስቃሴ በቅርበት የሚመራውን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አፈጻጸም  የሚከታተል ፣የሚገመግም  እና የውሳኔ ሃሳቦችን በማሳለፍ የጥምረቱን የስራእንቅስቃሴ የሚያሳልጥ ጠቅላላ ጉባኤ በከተማና በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚኖረው ሲሆን የጠቅላላ ጉባኤው ስብጥር በሚከተለው መሰረት የሚዋቀር ይሆናል፡፡

### 6.1. የጠቅላላ ጉባኤው ስብጥር

#### 6.1.1. በከተማ ደረጃ

1. በከተማ ደረጃ የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት--------11
2. የክፍለ ከተማ የክበባት ጥምረት ሰብሳቢዎች-------------------11
3. የወረዳ ክበባት ጥምረት ሰብሳቢዎች------------------------------113
4. የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ስራአስኪያጆች---------113
5. የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ተወካይ--------------1
6. የወጣቶች ምክርቤት ተወካይ----------------------------------------1
7. የሲቪክ ማህበራት ማደራጃ ተቋም ተወካይ-----------------------1
8. የከንቲባ ጽ/ቤት ተወካይ-----------------------------------------------1
9. የትምህርት ቢሮ ተወካይ-----------------------------------------------1
10. የጤና ቢሮ ተወካይ--------------------------------------------------------1
11. የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ተወካይ---------------------------------1
12. የአዲስ አበባ ባህል፤ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ተወካይ---------------1
13. የምግብ፤መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ተወካይ---1
14. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ተወካይ--------1

15. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ተወካይ----------1
16. የአዲስ አበባ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ተወካይ------1
17. የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ተወካይ-------------1
18. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ተወካይ---------------------------------1
19. የአዲስ አበባ ምክርቤት ተወካይ--------------------------------------------------------------1
20. ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ-------------------------------------------------------1

### 6.1.1. በክፍለ ከተማ ደረጃ

21. በክ/ከተማ ደረጃ የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት--------11
22. የወረዳ ክበባት ጥምረት ሰብሳቢዎች------------------------------እንደ ወረዳው ብዛት
23. የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ስራአስኪያጆች---------እንደ ማዕከላቱ ብዛት
24. የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተወካይ--------------1
25. የወጣቶች ምክርቤት ተወካይ----------------------------------------1
26. የዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ተወካይ-----------------------------------------------1
27. የትምህርት ጽ/ቤት ተወካይ-------------------------------------------------1
28. የጤና ጽ/ቤት ተወካይ--------------------------------------------------------1
29. የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ተወካይ----------------------------------1
30. የአዲስ አበባ ባህል፤ኪነጥበብና ቱሪዝም ጽ/ቤት ተወካይ---------------1
31. የምግብ፤መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ጽ/ቤት ተወካይ---1
32. የገቢዎች ጽቤት ተወካይ----------1
33. የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ተወካይ-------------1
34. ስፖርት ጽ/ቤት ተወካይ----------------------------------1
35. የክፍለ ከተማው ምክርቤት ተወካይ-------------------------------------------------------------------1
36. ፖሊስ ጽ/ቤት ተወካይ-------------------------------------------------------------1

**የጠቅላላ ጉባኤው ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ/. ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

ለ. የጥምረቱን ስራአስፈጻሚ አባላት ይመርጣል ፤ይሽራል፡፡

ሐ. በአመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባዔ ያካሒዳል፤ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

መ. የጥምረቱን ዐመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያጸድቃል፡፡

ሠ. የጥምረቱን የስራ ክንውን ሪፖርት ያዳምጣል፤ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ረ. ከጥምረቱ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ይመረምራል፤ይወስናል፡፡

ሰ. አጠቃላይ የጥምረቱን እንቅስቃሴ ይመራል፤ይቆጣጠራል፡፡

ሸ. የሂሳብ መርማሪ ኦዲተር ይሾማል፡፡

ቀ. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስራ ክፍፍል ኃላፊነትና ተግባር ሊያወጣ ይችላል፡፡

**የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ፤ምልአተ ጉባዔና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት**

ሀ. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የሚመራው በጠቅላላ ጉባዔው በተመረጠ ሊቀመንበር /ተወካይ/ ይሆናል፡፡

ለ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

ሐ. ጠቅላላ ጉባዔው የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉ በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡እኩል ድምጽ በሚኖርበት ወቅት ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

መ. የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ አካል

የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰየሙ ሆነው አስራ አንድ የስራአስፈጻሚ አባላት የሚኖሩት ሲሆን አባላቱ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተመላክተዋል፡፡

7.1. **በከተማ ደረጃ**

ሀ/. የጥምረቱ ፕሬዚደንት----------ሰብሳቢ

ለ/. የጥምረቱ ም/ፕሬዚደንትና የክበባት ልማት ጉዳዮች ኃላፊ----------ም/ሰብሳቢ

ሐ/. የጥምረቱ ጸሀፊ---------------አባል

መ/. የጥምረቱ ገንዘብ ያዥ ---------አባል

ሠ/. የሂሳብ ሹም ------አባል

ረ/.የንብረት ኃላፊ ------አባል

ሸ/.የሀብት አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ --------አባል

ቀ/. የህዝብ ግኙኙነት ጉዳዮች ሰብሳቢ--------አባል

በ/. የክበባት ውድድርና ተሳትፎ ጉዳዮች ሰብሳቢ-------አባል

ተ/.የውስጥ ኦዲት --------------አባል

ቸ/.የጥምረቱ አቅድና በጀት ኃላፊ-------አባል

**በክ/ከተማ ደረጃ**

በክፍለ ከተማ ደረጃ የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የወረዳው ጥምረት ሰብሳቢዎች የሚወከሉበት ሲሆን በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰየሙ ሆነው አስራ አንድ የስራአስፈጻሚ አባላት ይኖሩታል፡፡ አባላቱ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተመላክተዋል፡፡

ሀ/. የጥምረቱ ፕሬዚደንት----------ሰብሳቢ

ለ/. የጥምረቱ ም/ፕሬዚደንትና የክበባት ልማት ጉዳዮች ኃላፊ----------ም/ሰብሳቢ

ሐ/. የጥምረቱ ጸሀፊ---------------አባል

መ/. የጥምረቱ ገንዘብ ያዥ ---------አባል

ሠ/. የሂሳብ ሹም ------አባል

ረ/. የንብረት ኃላፊ ------አባል

ሸ/. የሀብት አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ --------አባል

ቀ/. የህዝብ ግኙኙነት ጉዳዮች ሰብሳቢ--------አባል

በ/. የክበባት ውድድርና ተሳትፎ ጉዳዮች ሰብሳቢ-------አባል

ተ/. የውስጥ ኦዲት --------------አባል

ቸ/. የጥምረቱ አቅድና በጀት ኃላፊ-------አባል

**በወረዳ ደረጃ**

የወረዳው የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በማዕከሉ የሚንቀሳቀሱ ክበባት ሰብሳቢዎች የሚወከሉበት ሲሆን በክፍለ ከተማው ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየሙ ሆነው አስራ አንድ የስራአስፈጻሚ አባላት ይኖሩታል፡፡ አባላቱ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተመላክተዋል፡፡

ሀ/. የጥምረቱ ፕሬዚደንት----------ሰብሳቢ

ለ/. የጥምረቱ ም/ፕሬዚደንትና የክበባት ልማት ጉዳዮች ኃላፊ----------ም/ሰብሳቢ

ሐ/. የጥምረቱ ጸሀፊ---------------አባል

መ/. የጥምረቱ ገንዘብ ያዥ ---------አባል

ሠ/. የሂሳብ ሹም ------አባል

ረ/. የንብረት ኃላፊ ------አባል

ሸ/. የሀብት አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ --------አባል

ቀ/. የህዝብ ግኝኙነት ጉዳዮች ሰብሳቢ--------አባል

በ/. የክበባት ውድድርና ተሳትፎ ጉዳዮች ሰብሳቢ-------አባል

ተ/. የውስጥ ኦዲት --------------አባል

ቸ/. የጥምረቱ አቅድና በጀት ኃላፊ-------አባል

## አንቀጽ ስምንት

## የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

ከጠቅላላ ጉባዔው ቀጥሎ ጥምረቱ የክበባት የበላይ አካል ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

1. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራሙን ዕቅድና በጀት ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡
2. ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡

3. የጥምረቱን ሀብትና ንብረት በግልጽነትና ተጠያቂነት ያስተዳድራል፤በህጋዊ ደረሰኝ ይመዘግባል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፡፡
4. ክበባትን ማልማትና ማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በትስስር ይሰራል፡፡
5. ክበባት ልምድና ተሞክሮዎቻቸውን የሚያጋሩባቸውና የሚያስተዋዉቁባቸውን መድረኮች ያመቻቻል፡፡
6. ክበባት በዘላቂነት የሚለሙባቸውን ስትራቴጂዎች ይቀይሳል፡፡
7. የጥምረቱን ተቋማዊ አቅም የሚያጠናክሩ አሰራሮችን ይቀይሳል፡፡
8. ሀገራዊና አለማቀፋዊ ልምድና ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ያስፋፋል፡፡
9. አባል ክበባትንና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ወጣቶች የጎጂ መጤ ልማዳዊ ድርጊቶችና መሰል ማህበራዊ ጠንቆች ተጋላጭ እንዳይሆኑ ትምህርትና ግንዛቤ ማስጨበጥ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ይሰራል፡፡
10. ክበባት በፋይናንስና ግብዓት እንዲደራጁ ይሰራል፡፡
11. ክበባት በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ልማት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይሰራል፡፡
12. ክበባት በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የበጎ ፈቃድ ባህል እንዲጎለብት ሚናዉን ይወጣል፡፡
13. የክበባት ዓመታዊ መዋጮ መጠን ይወስናል፡፡
14. በክበባት አሰራር ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
15. የክበባትን ውስጠ ደንብ ያጸድቃል፤ያሻሽላል፡፡
16. ለጥምረቱ አሰራርና ውሳኔ ተገዢ ያልሆኑ ክበባትን ከአባልነት ሊሰርዝ ይችላል፡፡
17. የስራአስፈጻሚው የስራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡ጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አስር

## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስልጣንና ተግባር፡፡

### 1. የጥምረቱ ፕሬዚደንት ስልጣንና ተግባር

ሀ/. የስራአስፈጻሚ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

ለ/. የስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ተግባራቸውን በተሰጣቸው ስራ ዝርዝር መሰረት ማከናወናቸውን ይከታተላል፡፡

ሐ/. ከገንዘብ ያዡ ጋር በጥምረት ይፈርማል፣አስፈላጊ ሲሆን የገንዘብ ወጪ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡

መ/. የጥምረቱ መመሪያዎችና አሰራር ስርዓቶች በስራአስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ተፈጻሚ መሆኑን ይከታተላል፡፡

ሠ/. ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ላይ ጥምረቱን በመወከል ይሳተፋል፡፡

ረ/. ጥምረቱን በመወከል ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

ሰ/. የጥምረቱን አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው ያቀርባል፡፡

ሸ/. ከጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡ አቅጣጫዎችን ተቀብሎ ያስፈጽማል፡፡

ቀ/. ክበባትን ማልማትና ማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ውይይት ያደርጋል፣ የስምምነት ፊርማ ይፈራረማል፣ ውል ይፈጽማል፡፡

በ/. የጥምረቱን ተቋማዊ አቅም የሚያጠናክሩ ስልቶችን ይቀይሳል፡፡

## 2. የምክትል ፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር

ሀ/. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

ለ/. ከስራአስፈጻሚ ኮሚቴና ከሰብሳቢው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ሐ/. ክበባት በዘላቂነት የሚለሙበትና የሚጠናከሩባቸውን ስትራቴጂዎች ይቀይሳል፡፡

መ/. ከፕሬዚደንቱ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራት ይፈጽማል፣

ሠ/. የጥምረቱን ማህተም ይይዛል፣

## 3. የጥምረቱ ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/. የጥምረቱን እቅድ ያቅዳል፣ ሪፖርት ያዘጋጃል፣የውይይት አጀንዳ ይቀርጻል፣ ቃለ-ጉባኤ ያደራጃል፡፡

ለ/. የጥምረቱን አባላት መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

ሐ/. ጥምረቱ የሚፈጽማቸውን የአጋርነትና ትብብር ሰነዶች ያዘጋጃል፡፡

## 4. የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/. በጥምረቱና በክበባት የተከናወኑ ተግባራትን ያስተዋዉቃል፡፡

ለ/. የጥምረቱንና ክበቡን ዓላማ ማስተዋወቅና መስገንዘብ የሚያስችሉ ጽሁፎች ፤መጽሄቶች፤ብሮሸሮች፤ፖስት ካርዶች፤ፖስተሮች፤ ፎቶ ግራፎችን የዘጋጃል፤ያሰራጫል፤

ሐ/. ጥምረቱና ክበባት ያከናወኗቸውን የስራ ውጤቶች በመድረክ ወይም በሚዲያ በየጊዜው የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

መ/. የጥምረቱንና የክበባትን እንቅስቃሴ ለህብረተሰቡ ማስገንዘብ የሚያስችሉ አውደ ርዕዮችን ያዘጋጃል፡፡

ሠ/. ለስራው ስኬታማነት አጋዥ የሆነ  3 አባላት ያሉት የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

## 5. የሀብት አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የጥምረቱንና የክበባትን ልማት ለማጠናከር የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፤ ስፖንሰሮችን ያፈላልጋል፡፡

ለ/. የገቢ ማስገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ልዩ ትእይንተ ህዝብ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ የህትመት ውጤቶችን በማሳተም ለአባላቱ ይሸጣል፡፡

ሐ/. ለስራው ስኬታማነት አጋዥ የሆነ  3 አባላት ያሉት የሀብት አፈላላጊ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

## 6. የክበባት ውድድርና ተሳትፎ ጉዳዮች ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/. የጥምረቱን አባል ክበባት በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በልዩ ልዩ የውድድር መድረኮች ያሳትፋል፤ ያወዳድራል፤ እውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ለ/. ክበባት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡

ሐ/. ክበባት ዓመታዊ የተሰጥኦ ውድድርና ፌስቲቫል እንዲያካሂዱ ያደርጋል፡፡

መ/. ለስራው ስኬታማነት አጋዥ የሆነ 3 አባላት ያሉት የውድድርና ተሳትፎ ጉዳዮች አስተባባሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

## 7. የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሳብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባር ያከናውናል፡፡

ሀ/. በገንዘብ ያዥ የተሰበሰበውን ገንዘብ በትክክል ባንክ መግባቱን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፡፡

ለ/. የጥምሩን ገቢና ወጪ ሰነዶች ያዘጋጃል፡፡

ሐ/. የጥምረቱን ገቢና ወጪ ሂሳብ እንዲመረመር ሰነዶችን ለኦዲተር ያዘጋጃል፡፡

መ/. የጥምረቱን አጠቃላይ ሂሳብ በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርት ለስራአስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

## 8. የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

1. የጥምረቱን ገንዘብ ህጋዊ በሆነ ደረሰኝ ይሰበስባል፡፡
2. የተሰበሰበውን ገቢ በወቅቱ ባንክ በማስገባት ወርሐዊ ሪፖርት ለሂሳብ ሹም ያቀርባል፡፡
3. በሰብሰቢውና በሂሳብ ሹሙ ፊርማ ሲታዘዝ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡፡

## 9. የንብረት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/. የጥምረቱን ንብረት ይመዘግባል፤በአግባቡ ስራላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ለ/. በስጦታ ፤በግዥ ወይም በውሰት የተገኘ ንብረት ይረከባል፡፡

ሐ/. ለክበባት የሚሰራጩ የድጋፍ ግብዓቶችን ያሰራጫል፡፡

## 10. የውስጥ ኦዲት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/. ጥምረቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ስለመያዙ ያረጋግጣል፡፡

ለ/. በሂሳብ መዛግብትና በገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ ረገድ ተቀባይነት ያላቸው የአሰራር ስርዓቶችን ስለመከተሉ ይመረምራል፤ያረጋግጣል፤ ሪፖርት ለፕሬዚደንቱ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ

## የገቢ ምንጭና የአባላት መዋጮ

ሀ/. ከጥምረቱ አባል ክበባት በሚሰበሰብ የምዝገባና ዓመታዊ ክፍያ፤

ሐ/. ሌሎች የገቢ ምንጮችን ስፖንሰርሺፕና ከተለያዩ ትርኢቶች፤ህትመት ሽያጮች የሚገኝ ገቢ፤

መ/. ከተለያዩ አጋር አካላት የሚገኝ ድጎማ፤

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## የጥምረት አባልነት መስፈርት

ማንኛውም በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከልና በትምህርት ቤቶች ተደራጅተው መስራት የሚፈልጉና በመስራት ላይ የሚገኙ ክበባትን በአባልነት መታቀፍ የሚችሉ ሲሆን የአባል የመሆን ፍላጎት ያለው ክበብ

ሀ/.የጥምረቱን ዓላማ የተቀበለ ክበብ

ለ/. ዓመታዊ መዋጮ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ ክበብ፤

ሐ/. ለጥምረቱና ለማዕከሉ የሙያ ወይም የጉልበት፤የእውቀትና የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ፤

ሠ/. ለጥምረቱ ውስጥጠ ደንብ ተገዢ የሆነ ክበብ አባል ለመሆን ለጥምረቱ ማመልከቻ ሲያቀርብና የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ሲያጸድቅለት አባል መሆን ይችላል፡፡

ረ/. በስራቸው------------

## አንቀጽ አስራ ሶስት

## የጥምረቱ አባላት መብት

ሀ/. ሁሉም አባል ክበባት እኩል መብት አላቸው፤

ለ/. የመምረጥ፤የመመረጥ፤ስለጥምረቱ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፤

ሐ/. በጥምረቱ ስብሰባ የመገኘት፤ስለጥምረቱ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው፤

መ/. አባል ክበባት ያላቸውን ልምድ በመጠቀም በተሰማሩበት ዓላማና ዘርፍ ስራቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ጥምረቱ ከሚያገኘው ጥቅምም እኩል ተካፋይ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት

## የጥምረቱ አባል ክበባት ግዴታ

ሀ/. ማንኛውም አባል ክበብ የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ መክፈል አለበት፡፡

ለ/. አንድ አባል ክበብ ከጥምረት አባልነት የሚወጣው ወይም የሚሰናበተው የሚፈለግበትን እዳ መክፈል እና የተረከባቸውን የጥምረቱን/የማዕከሉ ንብረቶች ማስረከብ ካልቻለ ወይም ለጥምረቱ አሰራርና መመሪያ ተገዢ ሆኖ ካልተገኘ ነው፡፡

ሐ/. ማንኛውም አባል ክበብ የጥምረቱን ዓላማ የማክበር፣ማስከበር፣የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

መ/. አባል ክበባት በስነ-ምግባር የታነጹና የማዕከሉን እንዲሁም የጥምረቱን ደንብና መመሪያ አክብረው የሚንቀሳቀሱ መሆን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## የአባላት መዋጮ አከፋፈል ስርዓት

1. የመመዝገቢያ ክፍያ፣አመታዊ መዋጮ መጠንና አከፋፈል በጥምረቱ ይወሰናል፡፡
2. አዲስ ተመዝጋቢ ክበብ ወደ ጥምረቱ ለመግባት ፍላጎት ኖሮት ጥያቄ ሲያቀርብ በጥምረቱ በሚወሰን የአከፋፈል መጠን ከነመመዝገቢያው በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ አባል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት

## አባልነት የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች፡፡

አንድ አባል ክበብ በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሰረት ወይም ሌላ አጥጋቢ ምክንያት ሲኖር ከጥምረቱ ለመውጣት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡ ስንብቱ በጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ ሊወሰን ይችላል፡፡ ከዚህ ውጪ በሆነ ሁኔታ ከጥምረቱ የሚሰናበተው ፡-

1. ክበቡ የጥምረቱን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ ተሳትፎ ሲገኝ፣
2. ለጥምረቱ ዓላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚጠበቅበትን ተሳትፎ ካላደረገ ወይም የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚቃረን ወይም የሚገታ ተግባር ሲፈጽም፣
3. መዋጮውን ለሁለት ዓመት ያህል ጊዜ በተከታታይ ያልከፈለ ከሆነ፣
4. በራሱ ፈቃድ ከጥምረቱ ለመልቀቅ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣
5. ክበቡ ሲፈርስ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## የአባላት መዋጮ

ሀ/. አባል ክበባት የጥምረቱ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ በሚወስነው ውሳኔ መሰረት መመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ለ/. አዲስ ተመዝጋቢ ክበባት ጥምረቱ ያስቀመጠውን የእያንዳንዱ አባል ክበብ አማካይ ድርሻ ተሰልቶ ከነመመዝገቢያው በጥምረቱ በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ ይጠናቀቃል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት

## ውስጠ ደንብ ስለማውጣት

የጥምረቱ ውስጠ ደንብ በስራ ሂደት ያስከተለው ችግር ከክበባት በሚመነጩ ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ወይም ስራ አስፈጻሚው ሊሻሻሉ ይገባቸዋል የሚላቸውን በስድስት ወር በሚጠራው ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ከጸደቀ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- *ይህንን መመሪያ የሚቃረን ውስጠ ደንብ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡*

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ

## ክበብን ስለማፍረስ

ክበቡ የተቋቋመበትን ዓላማ መፈጸም ሲሳነው ወይም ከጥምረቱ አላማ ጋር ተጻራሪ እንቅስቃሴ ሲያደርግና ለጥምረቱ ህግና ስርዓት ተገዢ ካልሆነ ጠቅላላ ጉባኤው 2/3ኛው ድምጽ ክበቡ እንዲፈርስ ሲያስተላልፍ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የክበባት መብትና ግዴታ

### 1. የክበባት መብት

ሀ/. በጥምረቱ አባልነት የመሳተፍ መብት አላቸው፤

ሐ/. ጥምረቱ የሚያዘጋጃቸውን ልዩ ልዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን፣የተሞክሮ ልውውጥ መድረኮችን የማግኘት መብት አላቸው፣

መ/. ጥምረቱ በፕሮጀክት ተቀርጸው የሚገኙ፣ በስፖንሰርሺፕ የሚገኙና ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ የሚመነጩ ሀብትና ንብረቶች እኩል የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

ሠ/. አባል ክበባት ጥምረቱ በሚያዘጋጃቸው የውድድር፣የአውደ ርእይ፣ የፌስቲቫል፣የፓናል ውይይቶችና ልምድ ልውውጦች የመሳተፍና ስራዎቻቸውን የማስተዋወቅ መብት አላቸው፡፡

## 2. ክበባት ግዴታ

ሀ/. የጥምረቱን  ህግና ስርዓት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

ለ/. የጥምረቱን ሀብትና ንብረት የመንከባከብ፣ በአግባቡ የመጠቀምና ለማዕከሉ አገልግሎት አስፈላጊ በሚሆኑበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

ሐ/. ጥምረቱ በሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የመሳተፍና አባሎቻቸውን የማስተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

መ/. አባል ክበባት ዕቅድና ሪፖርታቸውን ለጥምረቱ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም በወጣቶች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት ጥምረቱ ተግባሩን በሚያከናውንበት በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በአውጪው መስሪያቤት አማካኝነት ወደፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሻሻል ይችላል፡፡

**አንቀጽ ሃያ ሶስት**

**ይህ መመሪያ ከ-----------------ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡**

**አብረሃም ታደሰ ካሳዬ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ**